# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ 21-31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከፌብሪዋሪ 1-10/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌብሪዋሪ 2023
አዲስ አበባ

ርዕስ　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　ገፅ


እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ....... 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....... 2

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....... 3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ....... 4

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....... 4

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ....... 5

በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 5

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታበውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 6

እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2023 የሚኖረው የአየር ....... 7

ሁኔታ አዝማሚያ ....... 7

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1-10 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....... 7

ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1-10 የሚኖረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ ....... 7

እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2023 የሚኖረው የአየር ....... 8

ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 8

እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 8


# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በጃንዋሪ ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አመዝኖ ተስተውሏል። ሆኖም በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናት በተወሰነ መልኩ ወደ ሀገራችን ይገባ ከነበረው እርጥበት አዘል አየር ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን መጨመር ነበር። በመሆኑም በደቡብ በምዕራብ ኢትዮጵያ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ኪስ ቦታዎች ላይ ቀላል ዝናብ ተመዝግቧል። በሌላ በኩል ከነበረው የደመና ሽፋን መጨመር ጋር በተያያዘ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ጋብ ብሎ ተስተውሏል። ይሁን እንጂ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ክፍሎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የአየር ሙቀት ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ነበር። ለመጥቀስ ያህል በአርሲ ሮቤ 2.2፣ 3.5 እና 4.0፣ በአደሌ 4.0፣ በሀሮማያ -1.4፣ 2.4፣ 2.8 እና 3.0 በአምባ ማርያም 4.2፣ 4.4 እና 4.6፣ በደብረብርሃን 3.4፣ በዳንግላ 2.5፣ 3.0፣3.5 እና 4.0፣ በደባርቅ 4.5፣ በእምድብር 4.8፣ በመሀል ሜዳ 1.5፣ በወገል ጤና 2.8፣ 3.2.፣ 3.5 እና 3.6 እንዲሁም በባሌ ሮቤ 4.0 በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል።


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ በመቆየቱ የተነሳ እምብዛም ዝናብ አልነበረም ማለት ይቻላል። ይሁንና በደቡብ በምዕራብ ኢትዮጵያ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ኪስ ቦታዎች ላይ ከተመዘገበው 5-67 ሚ.ሜ. የሚደርስ መጠን ያለው ዝናብ ከ 2-4 ቀናት ያህል የተመዘገበ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል (ካርታ 1 እና 2) ።

በዚሁ መሠረት በአሥሩ ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመደበኛው በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ካርታ 3) ።


ካርታ 1   ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   ከ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች    መደበኛ    ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የጃንዋሪ ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት የነበረው የአየር ሁኔታ ለመኸር አብቃይ በሆኑት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመካሄድ ላይ ላለው ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ከደረቃማውና ከነፋሻማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይሁን እንጂ በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናት በተወሰነ መልኩ ወደ ሀገራችን ይገባ ከነበረው እርጥበት አዘል አየር ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ  የደመና ሽፋን በመጨመሩ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ጋብ ብሎ ተስተውሏል። በሌላ በኩል ጥቂት ቀናት በተወሰነ መልኩ አልፎ አልፎ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑ የጥምር ግብርናን በሚያከናውኑ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በጥቂት ስፍራዎቻቸዉ ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የተመዘገበ ሲሆን ይህም የተገኘዉ እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት በተወሰነ መልኩ በጎ ገጽታ ነበረው  (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታበውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፈናቸው የጃንዋሪ የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት በአብዛኞዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ፡፡ ሆኖም በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናት በደቡብ በምዕራብ እና በደቡብ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከነዚህም በጥቂት የላይኛው ባሮ አኮቦ እና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ


በመደበኛ ሁኔታ በፌብሪዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚስተዋለው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት በስተቀር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማው የአየር ሁኔታ ያመዝናል፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር እንደሚኖራቸው  የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ስለሆነም ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ጉጂና ቦረና ዞኖች፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በሚገኙ የቤንች ማጂ፣ ሀዲያ፣ ወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞና ጎፋ ዞኖች፤ ሰገን ህዝቦች፤ ከደቡብ ምዕራብ ክልል የከፋ ዞን፤ ሲዳማ ክልል፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 3 ና 5፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ ዞን ቀላል ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1-10 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1-10 የሚኖረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ

## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የፌብርዋሪ የመጀመሪያዉ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማ የእርጥብት ሁኔታ የሚያመዝን ቢሆንም፤ በተወሰኑ የደቡብ ምዕራብ እና የደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች መጠነኛ እርጥበት የሚያገኙበት ወቅት ነው። እንዲሁም የበልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ለበልግ ስራ እንቅስቃሴ ዝግጅት የሚጀምሩበት ጊዜ ነው። ከላይ በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥሉት የፌብርዋሪ የመጀመሪያዉ አስር ቀናት የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር እንደሚኖራቸውና ከዚሁም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ የተወሰነ መጠን ያለው እርጥበት ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ ወቅት አምራች በሆኑት አካባቢዎች የሚገኘውን አነስተኛ እርጥበት በመጠቀም የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የበልግ ወቅት ሰብሎች አስቀድሞ በሚዘራባቸው አካባቢዎች ለማሳ ዝግጅት፣ ዘር ለመዝራት እና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት አቅርቦት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ይጠበቃል።

## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 10/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ፌብሪዋሪ አስር ቀናት የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች እርጥበት ማግኘት የሚጀምርበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በታችኛው ኦሞጊቤ፣ የላይኛዉ ባሮአኮቦ አዋሳኝ ተፋሰሶችና እንዲሁም በጥቂት የታችኛው የስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ መጠን እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ በተቀሩት በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሆነው እንደሚቆይ ይጠበቃል፡፡